# ሥርግውን ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት

ወዳጄን ጓደኛዬን ሥርግውን ለመጀመሪያ ጊዜ ያወቅሁት በቆሮንቶስ ከተማ ግሪክ አገር በ፲፱፻፵፮ ዓ. ም. ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እየተማረ ሳለ ነው። ከዚያም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቆ አቴና ዩኒቨርስቲ ለአምስት አመት ያህል አብረን ነበርን። ሥርግው ተቀምጦ ለብዙ ሰዓታት የሚያጠና የማይታክተው ተማሪ ስለነበር፣ እምብዛም አይዞርም ኳስም ሆነ ሌላ ጨዋታ ላይ አይታይም ነበር። በየፈተናውም ጥሩ ውጤት ያመጣም ስለነበር የኢትዮጵያን ተማሪዎች ጉብዝና የግሪክ መምህራንና ተማሪዎች እንዲያደንቁ አድርጎአል። በአዳሪ ቤት ግብር በጋራ ስንበላ ጎን ለጎን ተቀምጠናል። ሥርግው ቀስ ብሎ ስለሚበላ መጨረሻ ይቀራል። በርበሬ ይወድ ስለነበር አንዳንዴ ሲገኝ በብርቱካን እያጠቀሰ ሲበላና ስለሚያልበውም እንጠቃቀስበት ነበር።

ሥርግው ተማሪም ሆኖ ጠንካራ አቋም ይወስድ ነበር። በሀገሩና ለባህሉ ተቆርቋሪ በመሆኑ፣ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ላይ ቅያሜውን ሲገልጽ አስታውሳለሁ። ንጉሠ ነገሥቱ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን የፖለቲካ መሣሪያ አደረጉዋት በማለት ይቆጨው ነበር። ይህንም ንጉሠ ነገሥቱ በ፲፱፻፵፯ ዓ. ም. ግሪክን በጎበኙበት ጊዜ በይፋ ተናግሮታል። የንጉሠ ነገሥቱ አማች ደረጃ ኃይለማርያም አብሮ ስለነበረ ዘርዝሮ ነግሮታል። ጃንሆይም ወደ መስኮብ ለጉብኝት ከዚያው እንደሄዱ ለዚሁ ሰው በአሸሙር የቅዲስ ማርቆስ እርጥባን ይድረሳቸሁ ብሎ ጽፎለት ነበር።

ሥርግው ትምህርቱን ጨርሶ ቶሎ ተመልሶ እናቱንና ዘመዶቹን ለመርዳት ጉጉት ነበረው፣ ወስኖም ነበር። ሆኖም እናቱም አረፉ። እህቱም አረፈች። በ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. ለዕረፍት አዲስ አበባ መጥቼ ስለነበር ይህን ተረዳሁ። ስመለስም መርዶውን ይዤለት ሄድሁ። ለመንገር ጓደኞቹ ብዙ ተቸገርን። ሆኖም ደፍረን አረዳነው። ከዚያም፣ ትምህርቱን ግሪክ አገር እንደጨረሰ፣ ወደ ኢትዮጵያ የመምጣቱን አሳብ ሠርዞ ወደ ጀርመን አቀናና በቦን ዩኒቨርስቲ ተምሮ፣ እንደለመደው ሌት ተቀን በመስራት በአጭር ጊዜ ውስጥ በታሪክ በዶክተሬት ተመረቀና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመጀመሪው ኢትዮጵያዊ ታሪክ መምህር ሆነ። አብረንም ለብዙ ዘመናት በዚሁ ዩኒቨርስቲ አስተማርን። በ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ሳገባ ሥርግው ሙዜአችን ሆነ፣ ሁልጊዜ እናስታውሰዋለን።

በስደት ላይ እያለ ሆላንድ ላይደን ዩኒቨርስቲ ሲሠራ፣ የአጋጣሚ ነገር ሆኖ እኔ ጀርመን ቦን እሠራ ነበርና፣ በትልቅ አገልግል እንጀራና ወጥ ይዘን ከባለቤቴ ጋር ስንጎበኘው፣ ሆላንዳዊ የዩኒቨርስቲ መምህራን ጓደኞቹን ጠርቶ ተኩራርቶ ሲጋብዝ አስታውሰዋለሁ። ይህም በ፲፱፻፸፪ ዓ. ም. አካባቢ ነበር። ብዙም ሳይቆይ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ።

በግንቦት ወር በ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. እንደገና አገር ከመልቀቁ ሁለት ቀናት በፊት ከባለቤቴ ጋር ጎብኝተነዋል። ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁትም ያኔ ነው።

ኃይለ ገብርኤል ዳኜ
አዲስ አበባ